# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

20

★ ከተተፋ ኣይቀር

★ አርሶ አደሩ ፤ ትናንትና ዛሬ

★ ሴቶችና ቢሮክራሲ

★ ደም በደም ይነፃል

የካቲት ፲፩—፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

**ለውይይት መነሻ**

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፬ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው ።

# የርእዮተ ዓለም ትግል

፲፭ኛ ትምህርት ከን. ዓ

የሰዎች አስተሳሰብ የሚመነጨው ከተጨባጩ ኑሮዋቸው ነው ብለናል ። በጢሰኝነት ኑሮ እየተበዘበዘ የሚኖር ሰው ኑሮው ለውጥን ይፈልጋል ። አስተሳሰቡም እንደዚሁ ለውጥን ይፈልጋል። ባለርስት ሆኖ እየበዘበዘ የሚኖር ሰው ደግሞ ኑሮው ለውጥን አይፈልግም ። አስተሳሰቡም ለውጥን አይፈልግም ። ባጭሩ ሰዎች በኑሮዋቸው የተለያዩ ሲሆኑ በአስተሳሰባቸውም እንደዚሁ የተለያዩ ይሆናሉ ። በዚሁ መልክ ደግሞ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ መደቦችም እንደዚሁ በተለያየ ሁኔታ ሲኖሩ የተለያየ አስተሳሰብ ይኖራቸዋል ።

የአንድ ሰው አስተሳሰብ በብዙ አቅጣጫዎች የተሰበጣጠረ ነው ። የፖለቲካ እምነቱ ፤ ባህሉ፤ ፍልስፍናው፤ ሞራሉ ፤ ሥነ ጥበቡ፤ሥነ ጽሑፉ ... ወዘተ ሲጠቃለል ይህ ሰው በአጠቃላይ ስለኑሮ ያለውን አቋም ፤ ስለዓለም ያለውን አመለካከት ይሰጠናል ስለሆነም አንድ ሰው በነዚህ ሁሉ ነገሮች ያለው አስተሳሰብና አመለካከት ተጠቃሎ ፤ ተቀነባብሮ ርእዮተ ዓለም ይባላል ። በመደቦች በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ እያንዳንዱ መደብ የራሱ የሆነ ለጥቅሙ ለሚያደርገው ትግል በአጋዥነት የሚቀርብ በጠቅላላው ኅብረተሰብ ላይ ሊያነግሠው የሚፈልገው የመደብ ርእዮተ ዓለም አለው ። ግለሰቦችም ያላቸው ርእዮተ ዓለም የመደባቸው ርእዮተ ዓለም ነጸብራቅ እንጂ ከዚህ ወይም ከዚያ መደብ የማይጠቀስ ፤ ለዚህ ወይም ለዚያ መደብ ጥቅም የማይቆም የማያዳላና ገለልተኛ የሆነ ርእዮተ ዓለም የለም ።

በበዝባዥና በተበዝባዥ መደቦች በተከፈለ ማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ በዝባዥ መደቦች ብዝበዛቸውን ለመቀጠል ይታገላሉ ። ከፍ ብለን እንደተመለከትነው ይህንን ብዝበዛቸውንና የበላይነታቸውን ለማጽደቅ መንግሥት የሚባል ድርጅት እንዳላቸው አይተናል ። በመንግሥት አማካይነት ሕጋቸውንና ጥቅማቸውን ለማረጋገጥ ከመሞከራቸው ሌላ በርእዮተ ዓለም ደረጃም ተበዝባዦች ይህንን ሥርዓታቸውን ትክክለኛ ነው ብለው እንዲቀበሉ ፤ ዘለዓለማዊ ነው ብለው እንዲያምኑ፤ ለትግል እንዳይነሱና እንዳይጥሉት ለማድረግ የሚሞክር ርእዮተ ዓለም በኅብረተሰቡ ላይ እንዲሰፍን ያደርጋሉ ። በአንፃሩ ደግሞ ተበዝባዥ መደቦች ኑሮዋቸው ብዝበዛን ስለሚቃወም ያለውን ሥርዓት የሚቃወም ፤ መለወጥ እንዳለበት የሚያስተምር ፤ መለወጥ እንደሚቻል የሚያረጋግጥ ፤ ዘለዓለማዊ እንዳይደለ ፤ ግፈኛ እንደሆነ የሚያጋልጥ ተበዝባዦችን ወደትግል የሚጠራ ርእዮተ ዓለም ለማስፈን ይታገላሉ ።

እንግዲህ የመደቦች ትግል ሲባል በዚህም በርእዮተ ዓለም በኩል ያለውን ትግል ይጨምራል ማለት ነው ። በመደቦች በተከፈለ ኅብረተሰብ ውስጥም በመደቦች ትግል የማይሳተፍና የማያዳላ ሕግ፤ መንግሥት ፤ .... እንደሌለ ሁሉ በመደቦች ትግል

ውስጥ የማይሳተፍ ፍልስፍና ፤ ሥነ ጽሑፍ ፤ ሥዕል፤ ሙዚቃ ፤ ሞራል ፤ ... ወዘተ ሊኖር አይችልም ። ስለ ሆነም እያንዳንዱ ግለሰብ በፖለቲካ ፤ በፍልስፍና፤ ... በመሳሰሉ ጉዳዮች ሁሉ የሚሰነዝራቸው አስተ ሳሰቦች ሁሉ የመደብ ጥቅሙን የማያንጸባርቁ አቋ ሞች እንጂ እንዲሁም ካንጐሉ እየፈለቀ በዘፈቀደ የሚወረውራቸው ነገሮች አይደለም ።

ሌኒን እንዳለው ከእያንዳንዱ የሞራል ፤ የሃይ ማኖት ፤ የፖለቲካና የሶሻል አቋም በስተጀርባ በት ግል ላይ ካሉት መደቦች የዚህን ወይም የዚያን ጥቅም ማየት እስካልቻሉ ድረስ ሰዎች ዘለዓለማ ቸውን የተሞኙትን ያህል ወደፊትም ዘለዓለማቸ ውን ይሞኛሉ። ስለሆነም አንድ ሰው ተነሥቶ አንድ አስተያየት ሲሰነዝር ይኸ አስተያየት በደፈናው ልክ ነው ወይም ልክ አይደለም የሚባልበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም ። እዚያው በዚያው ለገዥ መደ ቦች ትክክል የሆነ ርእዮተ ዓለም ሁሉ ገዥ መደ ቦች ጥሩ የሆነ አቋም ሁሉ ለተገዥ መደቦች መጥፎ ርእዮተ ዓለምና አቋም ነው ። በአንፃሩ ደግሞ ለነሱ መጥፎ የሆነ ርእዮተ ዓለምና አቋም ሁሉ ለኛ ጥሩ ነው ማለት ነው ። ማኦ ሴቱንግ ለዚህ ነው በዚህ ትግል ውስጥ «ጠላት የሚቃወመውን ሁሉ መደ ገፍ አለብን ፤ ጠላት የሚደግፈውን ሁሉ መቃወም አለብን» ያለው ።

መንግሥት የሚባለው ድርጅት የማያዳላና ለኅብረተሰቡ በሙሉ የቆመ ነው እንደሚሉት ሁሉ አድኃሪዎች የርእዮተ ዓለምን አዳይነትና የመ ደብ ይዘትም ይክዳሉ ። አንድ ሰው ለምሳሌ የሚ ያስፋፋው ፍልስፍና ፤ የሚስለው ሥዕል ፤ የሚደር ሰው ሥነ ጽሑፍ የሚመስለውንና የሚታየውን የሚ ያንጸባርቅበት ፤ የአንድን መደብ ጥቅም ለመጠበቅ የሚረዳ መሆኑን ይክዳሉ ። ማርክሲስቶች ግን የነሱ ርእዮተ ዓለም ለጠቅላላው ኅብረተሰብ የሚበጅ ሳይሆን ለተበዝባዥ መደቦች ጥቅም የቆመ ፤ ለነሱ ብቻ የትግል መሣሪያ እንደሆነ ያምናሉ ስለሆ ነም ማርክሲዝም ጭቁን መደቦች በአድኃሪዎች ላይ ድልን ተጐናጽፈው አዲስ ኑሮ እንዲጀምሩ አብዮታዊ በሆነ ርእዮተ ዓለም እየታነፁ መታገል አለባቸው ይላል ።

ስዚህ ትግል አድኃሪዎች አድኃሪ ርእዮተ ዓለማቸውን በማስፋፋት በልዩ ልዩና የተሰበጣ ጠሩ ዘዴዎች ይጠቀማሉ ። ገዥ መደቦች ሃይ ማኖት ፤ ሞራል ፤ ሥዕል ፤ ሙዚቃ ፤ ሥነ ጽሑፍ ፤ ቴያትርና የመሳሰሉት ሁሉ አድኃሪ ርእዮተ ዓለማ ቸውን እንዲያስፋፉላቸው ፤ አካባቢያቸውን በነሱ አስተሳሰብና መልክ እንዲቀርጹላቸው ይታገላሉ ተገዥ መደቦች ደግሞ ከነዚሁ ውስጥ ለትግላ ቸው የሚያገለግሉትን ይቃወማሉ ፤ ለትግላቸው መሣሪያ የሚሆኑትን ደግሞ ይገለገሉባቸዋል ።

በዚህ አንፃር ሲታይ እንግዲህ አድኃሪዎች ለትግላቸው እንዲያግዛቸው የሚያስፋፉት ሞራል ወይም ግብረገብነት አለ ። አብዮታውያንም እንደ ዚሁ የአድኃሪዎችን ሞራል የሚቃወም የራሳ ቸውን ትግል የሚያግዝ አብዮታዊ ግብረ ገብነት አላ ቸው ። አድኃሪዎች በሥዕል ፤ በሙዚቃ ፤ በሥነ ጽሑፍ . . . . የሕዝቡን ትግል ለማፈን ይታገላሉ ። አብዮታውያን ደግሞ በነዚሁ በሥዕል ፤ በሙዚቃ በሥነ ጽሑፍ የሕዝቡን ትግል ለማፋፋም ይታ ገላሉ ። በዚህ መልክ በርእዮተ ዓለሙ መስክ በበዝ ባዦችና በተበዝባዦች ፤ በአድኃሪዎችና በተራ ማጆች መሀከል የሚያደርገው ትግል እጅግ የተወ ሳሰበና የተሰበጣጠረ ነው ። እስቲ አንዳንድ ምሳ ሌዎችን በመጥቀስ በስዕል ፤ በሙዚቃ ፤ በሥነ ጽሑፍ በሞራል . . . . የርእዮተ ዓለም ትግል እንዴት እን ደሚካሔድና እነዚህ ሁሉ እንዴት በመደቦች ትግል እንደሚሳተፉ እንመልከት ።